# ሠመር ራይዝ/Summer RISE 2024 የወላጅ/የሞግዚት ስምምነት Parent/Guardian Agreement

Department of Partnerships
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
850 Hungerford Drive, Room 159, Rockville, Maryland 20850

## PARENT/GUARDIAN/ELIGIBLE STUDENT CONSENT የወላጅ/ሞግዚት/ብቁ ተማሪ ስምምነት

ይህ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም/Summer RISE Program የተነደፈው በአሁኑ ወቅት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በመከታተል ላይ ለሚገኙ 11ኛ ክፍል ለገቡ እና 12ኛ ክፍል ለሚገኙ ተማሪዎች በሠመር ወቅት የሙያ ሥራ ልምዶችን ለመቃኘት እንዲያስችላቸው ነው።

1. እርስዎ ወላጅ/ሞግዚት እንደመሆንዎ መጠን፥ በ 2024-2025 የትምህርት ዓመት በ MCPS 11ኛ ወይም 12ኛ ክፍል የሚገባ-የምትገባ ተማሪ ስለሚሳተፍበት-ስለምትሳተፍበት ሁኔታ የተስማሙ መሆንዎን በማረጋገጥ በመገንዘብ ተስማምተዋል።
2. ከጁን 24, 2024 ጀምሮ እስከ ጁላይ 26, 2024 የሚካሄደው የሠመር ራይዝ መርሃ ግብር እስከ 5 ሳምንታት ድረስ የሚዘልቅ እና ቢያንስ ለ50 ሰአታት በተግባር የሚሠራ ስራ መሆኑን ተገንዝቤአለሁ -በተመደብኩበት የንግድ ኩባንያ፣ ድርጅት፣ ኤጀንሲ፣ ተቋም፣ ("የሙያ ሥራ ልምድ የሚሰጥ አስተናጋጅ ድርጅት") ጣቢያ በመገኘት፣ ወይም ቨርቹዋል ("የሙያ ልምድ") ላይ የተመሰረተ የመማር እድል ነው። ተማሪው(ዋ) በቀን ከ8 ሰአት ያልበለጠ እና በሳምንት ከ40 ሰአት የማይበልጥ በስራ ልምምድ አስተናጋጅ ቦታ ላይ ያሳልፋል/ታሳልፋለች። የሠመር ራይዝ/Summer RISE ተሣታፊዎች ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ 7:00 AM በፊት አይጀምሩም ወይም ከ 6:00 P.M. በፊት ያጠናቅቃሉ። ተማሪዎች የገንዘብ ድጎማ ክፍያ ለማግኘት በፕሮፌሽናል ክህሎት እና በፋይናንሻል ትምህርት አውደ ጥናት ላይ መሳተፍ እና 50 ሰአቱን ማጠናቀቅ ይጠበቅባቸዋል። ከሙያ ልምድ ሰጪ ተቋም የሚመለከተው የሥራ ባልደረባ ("Career Experience Host Designee(s)") የሠመር ራይዝ ፕሮግራም " Summer RISE Program" ሲጠናቀቅ ተቀባይነት ያለው 50-ሠዓት የሙያ ልምምድ ማረጋገጫ ይሰጣል።
3. ሠመር ራይዝ ፕሮግራም/Summer RISE Program ላይ የሚሳተፉ ተማሪዎች በቅድሚያ በአካል ወይም ቨርቹወል ሙያዊ ክህሎት እና በፋይናንስ እውቀት አውደጥናት መሣተፍ እንዳለባቸው በመገንዘብ ተስማምቻለሁ። አውደ ጥናቱ የሚካሄደው ከሚፈለገው የፕሮግራም ሰአት በተጨማሪ ነው።
4. ሠመር ራይዝ ፕሮግራም/Summer RISE Program በአካል የሚሳተፉ ተሳታፊዎች ከያሉበት ቦታ የሙያ ልምምድ ወደሚያገኙበት ሥፍራ ለመመላለስ የመጓጓዣ አቅርቦት የራሳቸው ሃላፊነት መሆኑን ገብቶኝ ተስማምቻለሁ። "Youth Cruiser SmarTrip® Cards" በሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ይገኛል።
5. በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠመር ራይዝ ፕሮግራም ሠራተኞች ለተመዘገቡት ተማሪዎች በሙሉ ሙያዊ ትምህርት ልምምድ/Career Experience ለመስጠት የተቻላቸውን ጥረት ሁሉ ያደርጋሉ፣ የሆነ ሆኖ የሙያ ልምድ ለማግኘት ምደባ የሚደረገው የቦታ መገኘትን መሠረት በማድረግ ይሆናል። የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ሠራተኞች ተሳታፊ ተማሪዎችን በጅኦግራፊያዊ አመቺነት፣ በአካል እና/ወይም ቨርቹወል እንደአመቺነቱ ከተገኘው ኢንዱስትሪ ጋር ለማቀናጀት እንደሚሞክሩ በመገንዘብ ተስማምተዋል።
6. የሠመር ራይዝ ፕሮግራም-ስንክልና ያላቸው ግለሰቦች የትምህርት ደምብ "Individuals with Disabilities Education Act (IDEA)" እና በተጓዳኝ የሜሪላንድ ህግ መስፈርት በሚፈለጉት ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ዉስጥ አለመካተቱን በመገንዘብ ተስማምተዋል።
7. የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች መርሃ ግብራቸውን በቀጥታ ከፕሮግራሙ መጀመር በፊት ከስራ ልምድ አስተናጋጅ ተወካይ(ዎች) ጋር የማስተባበር ሃላፊነት እንዳለባቸው ተረድተዋል እና ተስማምተዋል። ተሳታፊው(ዋ) ከዚህ ሰአት ውጭ እንዲጀምር/እንድትጀምር ወይም እንዲጨርስ/እንድትጨርስ ከሙያ ሥራ ልምድ አስተናጋጅ ተወካይ(ዎች) ለትብብር መምሪያ አስቀድሞ ካልተገለፀ በስተቀር የሙያ ልምምድ ሰአት የሚከናወነው ከሰኞ እስከ አርብ ከጠዋቱ 7፡00 A.M. እስከ 6፡00 P.M. ድረስ ብቻ ነው። የሙያ ልምድ ተቀባይ አስተናጋጆች ተወካይ(ዮች) ከቀኑ 9፡00 P.M. በላይ የተማሪ ተሳትፎን ሊጠይቁ አይችሉም።
8. የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች ጥሩ የሥራና የሙያ ልምድ መቅሰም፣ መልካም ስነምግባር፣ ትክክለኛነት፣ ስነስርአት መጠበቅ፣ ሳይዘገይ ወዲያውኑ መሥራት፣ ብስለት፣ ተገቢነት ያለው አለባበስ፣ አግባብ የሆነ የቢዝነስ ስነ-ምግባር፣ ማሳየት እንደሚጠበቅባቸው እና ቨርችወል የሚሳተፍ/የምትሳተፍ ከሆነ፣ በቪድኦ እንደሚሆን እንደሚታወቅ በመገንዘብ ተስማምቻለሁ። የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች በሙያ ልምድ አሳታፊዎች አማካይነት የማይፈታ ጉዳይ ካጋጠማቸው ለሠመር ራይዝ ፕሮግራም ጽ/ቤት "Summer RISE program office" በኢሜይል summer-rise@mcpsmd.org ወይም በስልክ ቁጥር 240-740-5599 በመደወል ማሳወቅ አለባቸው።
9. በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ወቅት ለተማሪ ድጋፍ ለመስጠት እና ጥያቄዎች ሲኖሩ ለመፍታት የሠመር ራይዝ  አስተማሪ አገናኝ መኮንን እንደሚመደብ ተስማምቻለሁ ተስማምቻለሁ። አንድ ተማሪ በአካል በሚደረግ የስራ ልምምድ ለመሳተፍ ከመረጠ(ች)፣ የሠመር ራይዝ መምህር አገናኝ መኮንን ወይም የሰመር ራይዝ ሰራተኞች የተማሪው(ዋ)ን የሥራ ልምምድ በርቀት የመቆጣጠር አማራጭ ይኖራቸዋል።
10. የስራ ልምምድ የሚሰጡ አካላት የማጣራት እና/ወይም ክትባቶችን የመሣሰሉ ተጨማሪ መስፈርቶች ሊኖራቸው እንደሚችል በመገንዘብ ተስማምቻለሁ። ጁን 24, 2024 የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ከሚጀምርበት ቀን በፊት ማንኛውንም ተጨማሪ መስፈርቶችን ለማሟላት ከስራ ልምድ አስተናጋጅ/ተወካይ ጋር በቀጥታ መስራት የሰመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች ሃላፊነት ነው። አንድ ተማሪ የአስተናጋጁን መስፈርቶች ማሟላት ካልቻለ(ች)፣ ከተገኘ ሌላ እድል ይጠብቃል/ትጠብቃለች።
11. ተማሪው(ዋ) በአካል በሰመር ራይዝ ፕሮግራም ለመሳተፍ ከመረጠ(ች) ከኮቪድ-19 ጋር የተያያዙ ማናቸውም ገደቦች እንዳሉ ሆነው፣ ተማሪው(ዋ) በፈቃደኝነት እና በወላጆች/በአሳዳጊዎች ፈቃድ እንደሚሰራ/እንደምትሠራ በመገንዘብ ተስማምተዋል። በተቻለ መጠን፣ የሙያ ልምድ ተቀባይ አስተናጋጆች ተወካይ(ዮች) በሞንትጎመሪ ካውንቲ አስተዳደር እና በ MCPS የተቀመጡትን የኮቪድ-19 ፕሮቶኮሎች መከተል አለባቸው። ለኮቪድ-19 ለተጋለጠ(ች) ተማሪ MCPS ምንም አይነት ሃላፊነት እንደማይወስድ ተገንዝበዋል።
12. የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ለማግኘት ስለ ሠመር ራይዝ ፕሮግራም ልምዳቸው ቅድመ ዳሰሳ እና የፕሮግራም መጨረሻ ዳሰሳ ማጠናቀቅ እንዳለባቸው በመገንዘብ ተስማምተዋል።
13. የሙያ ዝንባሌ እና ችሎታን ከዝንባሌአቸው ጋር ለማመሣከር እንዲያመች የተማሪው(ዋ) መረጃ ለሙያ ልምድ ሰጪ/ተወካይ ይሰጣል። የሙያ ልምምድ ሰጪ/ተወካይ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎችን መረጃ የሚያገኙት እንደዝንባሌአቸው ለመመደብ እና/ወይም ከማን ጋር እንደሚቀናጁ ለማወቅ ስለሚረዳ ነው። ከሰመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች የሚሰበሰቡ መረጃዎች በሙሉ በሙያ ልምድ አስተናጋጅ ወይም ተወካይ በኩል ለማንኛውም ሶስተኛ ወገን እንደማያጋሩ በመገንዘብተስማምተዋል።

14. ሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች ፕሮግራሙን በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቁ በኋላ ፈንድ ከተገኘ ለፕሮግራም ወጪያቸው እንደ ማካካሻ የሚቆጠር አበል እንደሚያገኙ በመገንዘብ ተስማምተዋል። MCPS የሠመር ራይዝ መርሃ ግብር ሲጠናቀቅ የተማሪው(ዋ)ን የስታይፐንድ ክፍያ ቼክ ለማዘጋጀት የተማሪው(ዋ)ን የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ስም ቼኩን ለሚያዘጋጀው ባንክ ያስተላልፋል። የአበል (ስታይፐንድ) ክፍያ ቼክ በበቂ የገንዘብ ድጋፍ መገኘት ላይ የተመሰረተ መሆኑን ተረድቻለሁ፣ እና የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች ዝቅተኛውን የ 50-ሰአት መስፈርት ተሟልቶ ከተገኘ እና በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ፅ/ቤት ከተረጋገጠ በኋላ በፕሮግራሙ ማጠቃለያ ላይ ቼካቸውን ይወስዳሉ። ቼክ ለመውሰድ በጋራ የሚመች ጊዜ አስቀድሞ ቀጠሮ ማስያዝ ያስፈልጋል። የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች ወይም ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው ስለ ተማሪ አበል ክፍያ ጥያቄ ካላቸው summer-rise@mcpsmd.org ወይም 240-740-5599 በመደወል የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ጽ/ቤትን "Summer RISE Program office" መጠየቅ ይችላሉ።

15. የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች ፕሮግራሙ በሚጠናቀቅበት ጊዜ በሙያ ልምድ ሰጪዎች ዘንድ ሥራ ለመቀጠር የይገባኛል ጥያቄ ስለማይኖር እንደሠራተኛ ለመቀጠር ተስፋ ማድረግ እንደሌለባቸው በመረዳት ተስማምተዋል።

16. የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሣታፊዎች የሰመር ራይዝ ፕሮግራም ሙያዊ ትምህርት ልምምድ በሚያገኙበት ቦታ ተቀጣሪዎች ሊሆኑ እንደማይችሉ የሙያ ልምድ ሰጪዎች ከሠመር ራይዝ ተሳታፊዎች የሥራ እንቅስቃሴ ምንም አይነት የራሳቸውን ጥቅም አይወስዱም፣ አንዳንድ ጊዜ እንደውም ሥራቸው ሊስተጓጎል ይችላል። የሰመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች በቀጥታ በስራ ልምድ አስተናጋጆች ስራ ላይ እንደማይሳተፉ ወይም በመደበኛነት ወይም በተከታታይ (ፋይል ማዘጋጀት፣ ሌሎች የፅህፈት ስራዎች ወይም ደንበኞችን ማስተናገድ) እንደማይሰሩ በመገንዘብ ተስማምተዋል። የሙያ ሥራ ልምድ ሰጪዎች ለተማሪዎች ስለ ቢዝነሱ/ስለ ድርጅቱ እና በሥራ ድርሻቸው ላይ የሚያተኩሩ ኃላፊነቶች፣ እና ስለ ቢዝነሱ/የድርጅቱን የሥራ እንቅስቃሴዎች በሚመለከት ለተማሪዎች ሁሉ አቀፍ ግንዛቤ ይሰጧቸዋል። ተማሪው(ዋ)/ተማሪዎቹ እነዚህን ሥራዎች በመሥራት ጥራትን፣ ሙያን፣ እና ሥራ አስኪያጅ ወይም ማናጀር ውጤታማ ሆኖ የሚሠራበትን አሠራር እና በበርካታ የሥራ ቀጣሪ ድርጅቶች አካባቢ ለመጠቀም የሚያስችል ጠለቅ ያለ እውቀት ያገኛሉ።

17. የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊ ይህን የስምምነት ውል፣ በሙያ ልምድ አስተናጋጆች የተሰጡትን ደንቦች እና መመሪያዎች፣ ወይም ሌላ ማንኛውንም ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም የተሰጡትን ደንቦች ካላከበረ(ች) MCPS በሚወስነው መሠረት፣የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ሊቋረጥ የሚችል ሲሆን የአበል ድጎማውንም ለማግኘት ብቁ አይሆንም/አትሆንም።

18. እርስዎ ወላጅ/ሞግዚት እንደመሆንዎ መጠን፥ ለተማሪ የሠመር ራይዝ የሥራ ልምድ ሰጪው ተቋም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ድርጅት አለመሆኑን እንደነዚህ ያሉ ድርጅቶች የሙያ ልምድ አስተናጋጆች እንዲሆኑ የተመረጡት ለተማሪዎች በሚሰጡት የሙያ ልምድ ዕድል ጥራት ላይ በመመስረት ነው። የሙያ ልምድ ተቀባይ አስተናጋጆች ህጎችን፣ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎችን እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦችን የመገምገም እና የማረጋገጥ ሃላፊነት አለባቸው። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እና/ወይም የሰመር ራይዝ ፕሮግራም ሰራተኞች የስራ ልምድ ተቀባይ አስተናጋጆችን እና/ወይም የስራ ልምድ አስተናጋጅ ተወካይ(ዮች)ን አይቆጣጠሩም ወይም እንደማይከታተሉ በመገንዘብ ተስማምተዋል።

19. እርስዎ ወላጅ/ሞግዚት እንደመሆንዎ መጠን ተማሪው(ዋ) በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ከመሣተፉ(ፏ) ጋር በተገናኘ ምክንያት ምንም አይነት ተጠያቂነት ወይም ብልሽት ቢያጋጥም MCPS ተጠያቂ እንደማይሆን በመረዳት ተስማምተዋል።

## ተጨማሪ ስምምነት

ተማሪ ኦንላይን ሲመዘገብ- ወላጅ/ሞግዚት የሚከተሉትን የተስማሙ መሆናቸውን ተማሪው(ዋ) ማረጋገጫ ይሰጣል/ትሰጣለች፡-

- ❏ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ባልደረባ ወይም የሙያ ሥራ ልምድ ሰጪ ተቋምን የሚወክል አካል ተማሪው(ዋ) በሠመር ራይዝ ምዝገባ ወቅት የሰጠ(ች)ውን የ MCPS ያልሆነ ኢሜይል አድራሻ በመጠቀም ለተማሪው(ዋ) ኢሜል ሊያደርጉ ይችላሉ። ያለፈቃድ/ያለስምምነት ከሶስተኛ ወገን ወደ MCPS የተማሪ ኢሜይል አካውንት ኢሜይሎችን ለመላክ ስለማይቻል ተማሪው(ዋ) መሳተፍ አይችልም/አትችልም። ከሙያ አስተናጋጅ/ተወካይ የሚመጡ የኢሜይል መልእክቶች የሚገናኙት ከሠመር ራይዝ ጉዳዮች ጋር ብቻ ነው።
- ❏ MCPS የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ሰራተኞች ወይም የስራ ልምድ አስተናጋጅ ተወካይ ለተማሪው(ዋ) በሰመር ራይዝ የተማሪ መመዝገቢያ ቅጽ ላይ ከሠመር ራይዝ ፕሮግራም ጋር ተዛማጅ የሆኑ ጉዳዮችን ብቻ ከተማሪው(ዋ) በተሰጠው ስልክ ቁጥር በመጠቀም ሊደውሉለ(ላ)ት ወይም መልክት ለመላክ ይችላሉ።
- ❏ ተማሪው(ዋ) በሚሣተፍበት-በምትሣተፍበት ወቅት ቪድኦ ለመቀረጽ፣ ፎተግራፍ ለመነሣት፣ እና/ወይም ሪኮርድ እንዲደረግ/እንድትደረግ ተፈቅዷል። እነዚህ ምስሎች እና/ወይም ሪኮርድ የተደረጉ ነገሮች ስለ ሠመር ራይዝ ማስተዋወቅን ጨምሮ ምስሎቹን ለመጠቀም መጠየቅ ሳያስፈልግ ለተለያየ ዓላማ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ።  በዚህ መልክ ጠቀሜታ ላይ በመዋላቸው ተማሪው(ዋ) ምንም ካሣ አይከፈለውም/አይከፈላትም እና MCPS ሁሉንም ምስሎች፣ ቪድዮዎች፣ እና የተቀረጹ/የተቀዱ ነገሮችን እና ሪኮርድ የተደረጉ ወይም የተወሰዱ ሥራዎችን የመጠቀም መብት አለው። የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተማሪ በሠመር ራይዝ የሙያ ሥራ ልምምድ ወቅት ቪዲዮ እንዳይቀረጽ፣ ወይም ፎቶግራፍ እንዳይነሳ ለመንገር እባክዎ የሠመር ራይዝ ቢሮን summer-rise@mcpsmd.org በኢሜል ይጠይቁ። ወይም እስከ አርብ፣ ጁን 14, 2024 ድረስ በስልክ ቁጥር 240-740-5599 ይደውሉ።
- ❏ የሠመር ራይዝ ተማሪ በግል ወይም በስራ ተሽከርካሪ የሞያ ልምምድ አስተናጋጅ ተወካይ ወይም ከሠመር ራይዝ ሰራተኞች ጋር ከስራ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች በሚነዱ ተሽከርካሪዎች እንዲሣፈር/እንድትሳፈር ተፈቅዶለ(ላ)ታል፣ እናም በዚህ ምክንያት ለሚፈጠር ማንኛውም ጉዳት MCPS ተጠያቂ እንደማይሆን ተማሪ እና ወላጅ/አሳዳጊ በመመገንዘብ ተስማምተዋል።
- ❏ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም አበል የሚከፈልበትን ቼክ ለማዘጋጀት አስፈላጊ ስለሆነ የሠመር ራይዝ መርሃ ግብር ሲጠናቀቅ ቼክ ለሚያዘጋጀው ባንክ የተማሪው(ዋ)ን የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ስም ይሰጣል።

## ፊርማ

በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ለመሣተፍ የወላጅ/የሞግዚት ስምምነት መደረጉን ለማረጋገጥ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተማሪ በኤሌክትሮኒክስ ይፈርማል/ትፈርማለች። በምዝገባ ወቅት፣ ጁን እና ጁላይ 2024 ድንገተኛ አደጋ ቢያጋጥም ለማግኘት እንዲቻል የወላጅ/አሳዳጊ ስም፣ ስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ ያስፈልጋል።